# <u>ምሕረት ለነማ?</u>

ተኮላ መኮንን
Tekola Mekonen
tekolamekonen@yahoo.com

ባለፈው የቀድሞ የደርግ ባለሥልጣናት ምሕረት ይደረግላቸው የሚል አስተያየት መንሳፈፍ ሲጀመር፡ <u>ምሕረት ለማ? እንዴት?</u> ብዩ የግሌን አስተያየት በተለያዩ የድሕረ ገጾች ላይ ማስፈሬ ይታወሳል። ያንን ጽሑፍ በጻፍኩበት ሰዓት መንግሥት የተጠና የሕግ ውስብስብ ፈጥሮ እነዚህን ወንጀለኞች ባፋጣኝ ይፈታቸዋል የሚል እምነት አልነበረኝም። በትላንትናው እለት ባደባባይ ታድነው የታሰሩት የደርግ ወንጀለኛ ባለስልጣናትና ተባባሪዎቻቸው በጓሮ በር መለቀቃቸውን ስሰማ ግን ከልብ ማዘኔን ለመግለጽ ዛሬ እነሆ ተነሳሁ።

መንግሥት በሚያደርጋቸው የልማት ሥራዎቹ በመደሰት በልማት እርብርቦሽ ላይ መሳተፍ አለብን ብሎ የተነሳው ሁሉ ኢሕአደግ የወሰዳቸውን የፖለቲካ ውሳኔዎች በሞላ እሰየው በማለት ተቀብሎ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ይሆናል። ለልማቱ እርዳታን መንግሥት የሁሉንም ተሳትፎ ሲጠይቅ እሺ እንደ ተባለ ሁሉ በሌላው ጎን ደግሞ ለሚሰነዘሩ የሕዝብ አስተያየቶችም ሆነ ነቀፌታዎች ጆሮውን ይሰጣል በማለት ጭምር እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል። ከሁሉም በላይ ሕግ መከበር እንዳለበት የሕግ የበላይነት መሰመር ያለበትጉዳይ ነው፣ እየተባለ በተደጋጋሚ ከመሪዎቹ ሲነገር ስንሰማ ምንም ይሁን ምን በሕግ ማመን ከተጀመረ የብዙው ችግራችን መፍትሄ ይሆናል ብሎ በመቀበልም ጭምር ነበር።

አሁንም ፍስሃ ደስታም ሆነ ለገሰ አስፋው ከሕዝቡ የበለጠ ሊሰሙ ይገባል የሚል አመለካከት መንግሥት ይኖረዋል ብሎ መገመት ይከብዳል።

ታዲያ ኢሕአደግ መሳሪያ አንስቶ የተዋደቀው በዱር በገደሉ የተንከራተተው የነበረውን የፋሽስት መንግስት ለማንበርከክ ብሎም ከሥልጣን አውርዶ ፍትሐዊ፡ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማንገስ እንደሆነ ሲያስተምረን ቆይቶ ብዙዎች ለዚህ እምነት ሕይወታቸውን ሰውተው አጥንታቸውን ከስክሰው ሳለ ዛሬ እንደ ቀላል ተወስዶ በሕዝብ ላይ ግፍ የፈጸሙት ሲለቀቁ የሕግ የበላይነት ሲሻር ለምን እንደተሻረ የማሳወቅ ግዴታ የለብኝም ሊለን አይችልም።

<u>የመንፈሳዊ አባቶች በጠየቁት</u> መሰረት እየተባለ የይቅርታ መዝሙር ሲዘመር መስማት ደግሞ በጣም እያሳዘነ እየመጣ ነው። ባለፈው ጽሁፌ ለመጥቀስ እንደ ሞከርኩት የመንፈሳዊ አባቶች ይቅርታን የማስተማር ሃላፊነት ቢኖርባቸውም ሕግን የማስቀልበስ ሥልጣን ግን ሊሰጣቸው አይገባም እላለሁ። ትላንት ለተደረገው እልቂት ዝምታቸው እነሱም ገና ይቅርታ አልጠየቁምና። በይቅርታ የተሞላ አመለካከት ካላቸው መጀመሪያ በውስጣቸው ያለውን ችግርም በይቅርታ መፍታት ነበረባቸው ብሎ ሕዝብ ቢጠይቅም እውነት ስለሚሆን አባባላቸውን በተግባር ለማሳየት የራሳቸውን ድርሻ ቢወጡ መልካም ነው።

እነዚህ ተለቀቁ የተባሉት ፋሽስቶች ላደረጉት ጥፋት ደግሞ ይቅርታ መጠየቅ ያለባቸውና ይቅርታውን መቀበልም ሆነ እንቢኝ የማለት መብት ያለው ደግሞ መንግሥት ሳይሆን ሕዝብ መሆን ይኖርበታል። በዚህም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው ሕዝብ ደስተኛ አለመሆኑን ደግሞ በይፋ ማስታወቁን አባቶችም የካዱት ጉዳይ አይደለም። መንግሥት ከስልጣን ያባረራቸውን ከነሱ የተሻለ በመሥራትና በግብር በማሳየት፡ ድርጊታቸውን በበጎ ሥራ በመተካት ማጋለጥ እንጂ መባረራችሁ አግባብ አይደለም መታሰራችሁ በዛ እንዴት ሊላቸው ይችላላ። ወንጀለኞቹስ ቢሆኑ ከመታሰራችን በፊት በስልጣን በመቆየታችን ጥፋተኞች ይላሉ ብለንም አንጠብቅምና።

ለማለት የፈለኩት ጧሪ ልጁን በፋሽስት ጥይት የተነጠቀው ሕዝቡ ነው። ቤተሰቡ በፋሽስት ጥይት ተገድሎበት አባትና እናት አልባ የሆነው ሕዝቡ ነው። በልጅህ እሬሳ ላይ ጨፍር የተባለው ሕዝቡ ነው። ለተገደለበት ጥይት ክፈል የተባለው ሕዝቡ ነው። በፈላ ዘይት የተጠበሰው፣ በጉማሬ የተተለተለው ሕዝቡ ነው። ብልቱ የተቆረጠው በማህጸናቸው የተፈጨ ጠርሙስ የተነሰነሰባቸው የሕዝብ ልጆች ናቸው። ዓይናቸው በወስፌ የፈረጠው ጥፍራቸው የተነቀለው የሕዝቡ ልጆች ናቸው። እኔን ያየህ ተቀጣ ተጽፎባቸው ነፃ እርምጃ በሚል በየመንደሩ በየመንገዱ ያለፍርድ የተገደሉት የሕዝቡ ልጆች ናቸው። ካለፍርድ የተገደሉት የቀድሞ ባለስልጣናት፡ መንግሥት ልትገለብጡ ነው ተብለው ያለፍርድ የተረሸኑት ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የሕዝብ አካል ናቸው። በሽቦ የታነቁ በቡልዶዘር በተቆፈረ ጉድጓድ የተቀበሩት ወጣት ሸማግሌዎች ሕዝብ ናቸው። በየጥሻው ተጥለው በጅብ የተበሉ ውሻ አስከሬናቸውን የበጣጠቀው የሕዝቡን ልጆች ነው። የነዚህ ሰለባ ቤተሰቦች ደግሞ ዛሬ እንደ አምሳለቃ ለገሰ አስፋው የጡረታ አበል የላቸውም። እንደ ፍቅረስላሴ ወግደረስ የሞቀ ቤት አይጠብቃቸውም እንደ እንዳለ ተሰማ፡ ፍስሃ ደስታ ሱፍ አይሰፋላቸውም። መኪና አይቀርብላቸውም። መንግሥት እንደ አጀማመሩ የሕዝብ እንባ ጠባቂ የሕግ የበላይነትን አስፈፃሚ እንጂ ትላንት በሕዝብ ላይ ኢ ሰብአዊ ድርጊት ፈጽመዋል ያላቸውን ወንጀለኞች በደል የደረሰበት ሕዝብ እግዚኦ እያለ የሚለቅ ከሆነ ለብዙ አጠያያቂ ነገሮች በር እየከፈተ ነው። ለመሆኑማ እነዚህ የቀድሞ ባለስልጣናት ጥፋተኛ አይደለንም ዝንብ አልገደልንም በፍርድ ቤት ብለው ሲሳለቁብን የነበሩ መሆናቸው እንዴት ተዘነ?

ለምህረትማ ለምን ለዓመታት የፈጀ የፍርድ ቤት ክርክር አስፈለገ?

ልዩ አቃቢ ሕጉ የምንም ከማንም ተጽእኖ ውጭ ነው ተብሎ ተነግሮን ነበር።

እድሜ ልክ እስራት ሲፈረድባቸው በፍርዱ አልስማማ ያለውና ፍርዱን በሞት ያስቀየረው አቃቢ ሕጉ አልነበረምን?

ሕዝብን በመግደል በመጨረስ ወንጀል በጥፋተኛነት የተፈረደባቸውን አሽባሪዎች ከእስር ለቆ ሌሎችን በሽባሪነት እንዴት መክሰስ ይቻላል?

በነገራችን ላይ በሞት ተቀጥቶ እድሜ ይፍታህ በምህረት የተዛወረለት ሰው ሲለቀቅ ይህ የመጀመሪያ ይመስለኛል። አሁን እንደሚነገረን በእድሜ ይፍታህ ምህረት የተደረገላቸው በሕግ መሰረት እድሜ ይፍታህ የተፈረደበት ሰው ፳ ዓመት ከታሰረ በአመክሮ እንደሚፈታ ስለሚታወቅ ነው። የሚለው እውነት ከሆነና መንግሥት ይህንን እያወቀ ከሆነ ቅጣቱን የቀየረላቸው የድርጊቱን አስከፊነት እጅግ ያከብደዋል።

ለመሆኑ በሕገመንግስቱ ላይ በቀይ ሽብር ጉዳይ መንግሥት እጁን አያስገባም የሚለው አባባል እንዴት ተቀየረ?

ስለእውነት ለግንዛቤ ይሆን ዘንድ አንዳንድ ነገሮችን ልጥቀስ። የጉራጌን ክልል የአዲስ አበባን ከተማ በሬሳ ክምር የሞላው ታዋቂው ነፍሰገዳይ ገሥግሥ ከእስራት ሲፈታ ደስተኛ የሚሆን አለ ብለው የሚያስቡ ባለሥልጣናት ይኖሩ ይሆን? ካሉ ከሕዝቡ ጀሯቸው እርቋል እላለሁ። የሕግ የበላይነት እንጂ የይቅርታ መስፈር ስርአትን አይቀይስም። የመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ የሸሪያ ሕግ በሃገራችን የበላይነት እንዲኖረው አንፈልግም። ለዚህም ነው ሕገ መንግሥት የመተዳደሪያ መመሪያ እንዲሆን የተደረገው። ሕገ ደንቡ ሁሌ እንዲጎብጥ ከተደረገ ደግሞ በመሳብ ብዛት አንድም ይለጠጣል ካልሆነም ይበጠሳል።

ነገ አሁን በተጀመረው ስሌት መሰረት ፳ ዓመት ሲሞላው ሻለቃ መላኩ ተፈራ ሲፈታ ነው።

ይህ ደግሞ የቆየ ቀልድ አስታወሰኝ። ቀደም ባለ ጊዜ ነው። ከአዲስ አበባ ወደ ጎንደር በሚሄድ አውቶቡስ ላይ ከተሳፈሩት አንዱ የጎንደር ገበሬ አጎኑ የተቀመጠውን ተሳፋሪ ስሙንና የት እንደሚሄድ ይጠይቀዋል። ተሳፋሪው ስሙ መገርሳ መሆኑንና ወደ ጎንደር ከተማ እንደሚሄድ ይነግረዋል። ገበሬው ለምን ጎንደር እንደሚሄድ ይጠይቀዋል። መገርሳም አስተማሪ እንደሆነ ይመልስለታል። ገበሬው ምን ሊያስተምር እንደሚሄድ አሁንም ይጠይቀዋል መገርሳም አማርኛ ሲለው ገበሬው ከተቀመጠበት ተነስቶ እሪ በይ ጎንደር አለ ይሉ ነበረ። ገበሬው አማርኛን ለማስተማር ማንም አጥንቶ አስተማሪ እንደሚሆን መቀበል ቢከብደው ሊገርመን አይገባም። ይልቅስ የሻለቃን ተፈራን ማንነት የጎንደር ሕዝብ አንጠርጥሮ ስለሚያውቅ ዛሬ እኔም እንደ አርሶ አደሩ እሪ በል ጎንደር ልል ስነሳ በእግዚአታ ተቀበሉኝ። የፋሽስት ደርግ ባለስልጣናት ሰለባ የሆነውን የኢትዮጳያ ሕዝብም እንዲሁ እሪ በል ወገኔ ልበለው። ምናልባት የሚያዳምጥ ሊኖር ይችላልና።

መንግሥት ዛሬ ሊወጣቸው የሚገባው ብዙ ችግሮች ከፊቱ ተጋርጠው እያሉ የመንግስቱ ኃይለማርያም ግብረ አበሮች ችግር እንደ ፈተና ሊያቀርብልን አይገባውም። አገራችን ሰላም የሆነው እነዚህ ወንጀለኞች በመታሰራቸውና ከስልጣን በመውረዳቸው መሆኑን ደግሞ ለደቂቃም መዘንጋት የለብንም። ለገሰ አስፋውን ካልፈታችሁ ብሎ ሰላማዊ ሰልፍ የወጣ አላየንምና። የተራቡትን ከርሃብ ለማዳን፡ መሃይምነትን ከሃገራችን ለማጥፋት ሕዝቡ "በቀን ሰዎስት ጊዜ የሚመገብበትን" በህክምና የሚረዳበትን መንገድ ማጣደፉን መቀጠሉ ሰላምና እድገትን ያመጣል ብለን በማሰብ ሕግን ከመሻር ይልቅ በሕግ የምንዳኝበትን መርህ በመከተል የተጀመረው የልማት እርብርቦሽ እንዲቀጥል እንተባበር እንጂ የሚያለያይ አዲስ መፈክር እያመጣን አንቆራቆስ። ይህንን ለማድረግ ደግሞ መንግስት ባስቸኳይ ለምን ግለሰቦቹ እንደተለቀቁ በይፋ ተናግሮ ሕዝቡን ማሳመን ይኖርበታል። በግርግር ተፈተው ከሆነም መልሰው ፍርዳቸውን መጨረስ ይኖርባቸዋል እላለሁ።